ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 42 ግንቦት30 /2018 ዓ.ም

## በውስጥ ገፆች

ለኮሚሽኑ ሴት አመራርና ሠራተኞች “የሴቶች ሚና በሥነምግባር ግንባታ” በሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጠ

ገጽ 2

የተቀናጀ የሙስና መከላከል ስልቶች ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል አይነተኛ ሚና አላቸው!

ገጽ 6

መልካምነት ያለበት የህክምና ሙያ!

ገጽ 8

## የሚመረጡ ሰዎች በዛ ልክ ታምነው እጃቸውና ልባቸው ንፁህ ሆኖ ህዝባቸውን ማገልገል አለባቸው - ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)



የሚመረጡ ሰዎች በዛ ልክ ታምነው እጃቸውና ልባቸው ንፁህ ሆኖ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ህዝባቸውን ማገልገል አለባቸው! ሲሉ የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ተናግረዋል፡ ፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህን የተናገሩት በሰባተኛው ጠቅላላ ሀገራዊ ምርጫ ድምጽ ለመስጠት በተገኙበት የምርጫ ጣቢያ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት ነው፡፡ አያይዘውም ይህ ህዝብ የሚሻውን ወስኖ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ከመረጠ በኋላ የዚህን ታላቅ ህዝብ ውለታ ለመክፈል



ዝግጁ መሆን እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል፡፡እልህ፣ ቁጣ፣ ክርክር፣ አሸነፋለው፤ አልሸነፍም ሳይሆን ይህን ያመነና ራሱን የሰጠ ህዝብ ህይወት ለመቀየር የተመረጡ ሰዎች ሌብነትንና ስንፍናን ተጠይፈው፣ ራስ ወዳድነትን ጠልተው ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ከፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ የውስጥ ቁርጠኝነትን እንደሚጠይቅ አፅንኦት ሰጥተዋል፡፡ ያሸነፉ በታማኝነት እንዲያገለግሉ፤ የተሸነፉ ደግሞ ውጤቱን በፀጋ እንዲቀበሉ ያሳሰቡት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በምድር ታምኖ ማገልገል በሰማይም የታመነ ይሆናል ብለዋል፡

## የባንካችን አመራር ለጥቅም ግጭት አጋላጭ የሆኑ አሠራሮችን መለየትና ግጭቶችን በሕጋዊ አሠራር መከላከል ይገባቸዋል - አቶ እዮብ ገብረኢየሱስ





የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከፍተኛ አመራሮች “የከፍተኛ አመራሩ አርአያነት፤ ለፀረ-ሙስና ትግል ያለው ፋይዳ!” በሚል መሪ ቃል ስልጠናዊ ውይይት አካሂዷል፡፡ ሥልጠናውን በንግግር የከፈቱት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ አቶ እዮብ ገብረኢየሱስ እንዳሉት፣ ባንኩ ተቆጣጣሪ ተቋም እንደመሆኑ በሥነምግባር ለሌሎች ተቋማት በአርዓያነት የሚጠቀስ ስመጥር የማድረግ ኃላፊነት በተለይ ከአመራሩ ይጠበቃል ብለዋል፡፡

ወደ ገጽ 3 የዞረ

## ኮሚሽኑ በዘርፎች በተጠኑ የአሰራር ሥርዓት ጥናቶች ላይና በዲጂታል የሀብት ምዝገባ ዙሪያ ውይይት አካሄደ

የፌደራል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከዘርፍ ፎረም አመራሮችና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈጻሚዎች ጋር በ26 ዘርፎች በተጠኑ የአሰራር ሥርዓት ጥናቶች ላይና በዲጂታል የሀብት ምዝገባ ዙሪያ ውይይት አካሂዷል፡፡

በመድረኩ የተገኙት በኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናት ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ክቡር አቶ እሸቱ




አስፋው ባለፋት ዘጠኝ ወራት በሙስና መከላከል ሥራ ላይ ውጤታማ ተግባራት እንደተከናወኑ ገልፀው፤ በቀጣይ ወራትም በእቅድ የተያዙ ቀሪ ተግባራት መጠናቀቅ እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡ በውይይት መድረኩ በ26 ዘርፎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የአሰራር ሥርዓት ጥናት ሪፖርት በኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ገዛኸኝ ጋሻው አቅርበዋል፡፡ በቀረበው ሪፖርት ላይ ሰፊ ውይይት የተደረገ ሲሆን፥ በጥናቱ ላይ ጥሩ ስራዎችን የሰሩና ወደ ኋላ የቀሩ ዘርፎች ተገምግመዋል፡፡

ወደ ገጽ 2 የዞረ

**የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካልዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!**

## ለኮሚሽኑ ሴት አመራርና ሠራተኞች “የሴቶች ሚና በሥነምግባር ግንባታ” በሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጠ





ለፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሴት አመራርና ሠራተኞች “የሴቶች ሚና በሥነምግባር ግንባታ” በሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል። በመድረኩ የተገኙት በኮሚሽኑ የሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ክቡር አቶ ፍቃዱ ሰቦቃ ትውልድን በመልካም ሥነምግባር በማነጽ በኩል የሴቶች ሚና ከፍተኛ መሆኑን ገልፀው፤ ትውልድን በማስቀጠልና ሀገርን ወደ ብልፅግና ለማድረስም ድርሻቸው የጎላ ነው ሲሉ ተናግረዋል። ትውልድን በሥነምግባር ለመገንባትና ሙስናን ለመከላከል ቤተሰብ፣ የኃይማኖት ተቋማት እና የባለድርሻ አካላት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ለዚህም በተሰማራንበት የሥራ መስክ በሥነምግባራችን አርዓያ በመሆን ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ልንከላከል ይገባል ብለዋል።

በኮሚሽኑ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ አካቶ ትግበራ ሥራ አስፈፃሚ ወ/ሮ መንበረ እሸቱ በበኩላቸው፥ ሴቶች ለትውልድ ሥነምግባር ግንባታ መሠረት ናቸው ብለዋል። ሙስና ሕጻናትን፣ ቤተሰብን፣ የትምህርትንና የጤና ተቋማትን የሚጎዳ መሆኑን



ገልፀው፥ ችግሩን ለመከላከልም የሴቶች ሚና ከፍተኛ ነው ሲሉ ተናግረዋል። ስልጠናው በአገርዓቀፍ የፀረ-ሙስና ምርምር ትስስር አባል ተስፋዬ ሂርጳሳ (ዶ/ር) የተሰጠ ሲሆን፥ ከሰልጣኞች ጥያቄ፣ ሀሳብና አስተያየቶች ተነስተው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።



## የሥልጠና ጥራትና ተገቢነት ኮንፈረንስ ተካሄደ



የፌደራል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከዘርፍ ፎረም አመራሮችና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈጻሚዎች ጋር የሥልጠና ጥራትና ተገቢነት ኮንፈረንስ አካሂዷል። ኮንፈረንሱ ባለትፉት 9 ወራት የተሰጡ ስልጠናዎች ምን ያህል



ጥራትና ተገቢነታቸውን የጠበቁ ናቸው የሚለውን ለመገምገምና



በቀጣይ የሚሰጡ ስልጠናዎች ላይ የጋራ አቅጣጫ ለማስቀመጥ ነው።

በኮንፈረንሱ ባለፉት ወራት ሲሰጡ የነበሩ ስልጠናዎች ዘርፍ ተኮር በመሆናቸው ውጤታማና ችግር ፈች እየሆኑ




መምጣታቸው ተገልጿል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ለፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈፃሚዎች በተቀናጀ የሙስና መከላከያ ስልቶች ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል። በመድረኩም ከተሳታፊዎች ሀሳቦች፣ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተነስተው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።

## ኮሚሽኑ በዘርፎች በተጠኑ የአሰራር ሥርዓት ጥናቶች ላይና... ከ ገጽ 1 የዞረ





እንዲሁም በውይይት መድረኩ በተያዘው በጀት ዓመት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ጨምሮ በዘርፎች የተከናወነ የዲጂታል ሀብት ምዝገባ ሪፖርት በኮሚሽኑ የሀብት ምዝገባና የጥቅም ግጭት መከላከል መሪ ሥራ አስፈፃሚ ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር አቅርበዋል። በቀረበው ሪፖርትም እንደተመላከተው በዲጂታል ሀብት ምዝገባ ሥራ ጥሩና ደካማ አፈጻጸም ያላቸው ዘርፎችን በመለየት ለመገምገም ተችሏል። በመድረኩም ከተሳታፊዎች ሀሳቦች፣ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተነስተው በመድረኩ በተገኙ አመራሮች ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።





ፀረ - ሙስና

## የባንካችን አመራር ለጥቅም ግጭት አጋላጭ የሆኑ... ከ ገጽ 1 የዞረ



የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ዶክተር እዮብ ተካልኝ በሥልጠናው ላይ ባስተላለፉት መልዕክት፤ እያንዳንዱ የማኔጅመንት አባል በሥራ ክፍሉ ውስጥ ለጥቅም ግጭት የሚያጋልጡ አሠራሮችና



ሁኔታዎችን የመለየትና ክፍተቶችንም የመድፈን ኃላፊነት እንዳለበት አሳስበዋል። ብሔራዊ ባንኩ ዓለምአቀፍ ተወዳዳሪ ሊሆን የሚችለውን የፋይናንስ ዘርፍ የሚመራ ተቋም እንደመሆኑ፣ የባንኩ አመራር አባላትና ባለሙያዎች ዓለምአቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለውን ግልጽና ፍትሐዊ አሠራር ማስፈን እንደሚጠበቅባቸው አስምረውበታል።

በፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥልጠና መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ የኋላእሸት ደሳለኝ



በበኩላቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የአገሪቱን የፋይናንስ ዘርፍ የሚመራ እንደመሆኑ የጥቅም ግጭትን በመከላከል ረገድ ለሚቆጣጠራቸው አካላት ሁሉ መልካም ምሳሌ መሆን ይጠበቅበታል ብለዋል።



## ለኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ከፍተኛ አመራሮች ሥልጠና ተሰጠ



የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር "የከፍተኛ አመራሩ አርአያነት፤ ለፀረ-ሙስና ትግሉ ያለው ፋይዳ!" በሚል መሪ





ቃል ለኮርፖሬሽኑ ከፍተኛ አመራሮች በሥነ-ምግባራዊ የውሳኔ አሰጣጥ እና የጥቅም ግጭት መከላከልና ማስተዳደር ላይ ያተኮረ ሥልጠና ሰጥቷል።

በሥልጠና መድረኩ ላይ የኮርፖሬሽኑ ምክትል ሥራ አስፈጻሚ እና የሰው ሀብት ዘርፍ ኃላፊ ክቡር ዶክተር ውብሸት ሲሳይ ሙስናን መከላከል የሚጀምረው የግልና የተቋምን ዲሲፕሊን በማክበር ነው። ሙስና በባህሪው ከግል ዲሲፕሊን ግድፈት ጋር የሚያያዝ በመሆኑ ጥንቃቄ ማድረግና መምራት አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል። በሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ እና የጥቅም ግጭት መከላከል ዙሪያ የሚሰጠውን ሥልጠና በጥሞና ተከታትሎ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ አሳስበዋል።


የሥልጠናው ተሳታፊዎች በበኩላቸው እንደነዚህ ዓይነት ሥልጠናዎች በሥነ-ምግባር መሻሻል ላይ ያመጡትን ለውጥ በተግባር ለመፈተሽ ጉዳዩን በየጊዜው እየገመገሙ መሄድ ያስፈልጋል ብለዋል። የሙስና ወንጀልን በዘላቂነት ለመቀነስ ለሙስና አባባሽ ምክንያቶችን እንዲሁም አሠራሮችን አስቀድሞ በመዝጋት መከላከል እንደሚገባም ተገልጿል።



በመጨረሻም በሥልጠናው ዙሪያ ለተነሱ ጥያቄዎች በዕለቱ አሠልጣኝ ዶ/ር ዮሐንስ ጴጥሮስ በቂ መልስና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል። ከተነሱ ጥያቄዎችም ውስጥ "በየአገልግሎት መስጫ ተቋማት እየተስተዋለ ያለውን መጉላላት እና የእጅ መንሻ ጥያቄን ለማስቀረት ኮሚሽኑ ምን እየሠራ ይገኛል?" የሚል ሲሆን፣ ዶክተር ዮሐንስ ኮሚሽኑ ይህንን ሥልጠና እየሰጠ ያለው አመራሩ የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት ጉዳዩን ትኩረት ሰጥቶ በባለቤትነት እንዲመራው አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው ሲሉ አስረድተዋል።



## ለኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎችና ሹፌሮች በኢ-ፍሊት ማኔጅመንት ሥርዓት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጠ



ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥራ ኃላፊዎችና ሹፌሮች በኢ-ፍሊት ማኔጅመንት ስርዓት (e-FMS) ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል። የሥልጠናው ዓላማ ተሽከርካሪዎችን ለመቆጣጠርና ስምሪትን



እንዲሁም የነዳጅ አጠቃቀምን በቴክኖሎጅ በማስደገፍ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማስቻል ነው። ሥርዓቱ በተለይም የነዳጅ አጠቃቀምን ዲጂታል በማድረግ ለታለመለት ዓላማ እንዲውልና አላስፈላጊ ወጭን ለመቀነስ እንደሚያስችል ተገልጿል። ስልጠናውን የፌደራል የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ባለሙያዎች የሰጡ ሲሆን፣ ሰልጣኞች የተለያዩ ጥያቄዎችን፣ ሀሳቦችና አስተያየቶች አንስተው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።



# ቆይታ

**የኮሚሽኑን ስትራቴጂካዊ ዕቅዶች በማስተባበር፣ የውስጥ አሠራሮችን በማቀላጠፍና የተቋሙን ራዕይ በማሳካት ረገድ የኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት ሚና እጅግ ከፍተኛና ግንባር ቀደም ነው። በዚህ ዕትም በበጀት ዓመቱ የተመዘገቡ ዋና ዋና ስኬቶችን፣ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችንና የተወሰዱ የሪፎርም እርምጃዎችን በዝርዝር ለመቃኘት፣ ከፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የኮሚሽነር ጽ/ቤት ኃላፊ ከአቶ ተስፋዬ ሻሜቦ ጋር አጭር ቆይታ አድርገናል። አቶ ተስፋዬም ጽሕፈት ቤቱ ያለፈበትን የሥራ ሂደትና የወደፊት የትኩረት አቅጣጫዎችን አስመልክተው ማብራሪያ ሰጥተዋል። ለቃለ-ምልልሱ ፈቃደኛ ስለሆኑ በፀረ-ሙስና ጋዜጣ ስም ላቅ ያለ ምስጋና እናቀርባለን። መልካም ንባብ!**



አቶ ተስፋዬ ሻሜቦ የኮሚሽነር ጽ/ቤት ኃላፊ

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** ጽሕፈት ቤቱ በበጀት ዓመቱ ባለፉት ወራት ካቀዳቸው ዋና ዋና ግቦች ውስጥ ስኬታማ ነበሩ የሚሏቸውንና ለኮሚሽኑ ስኬት ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረከቱትን ዋና ዋና አፈጻጸሞች ቢገልጹልን?

**አቶ ተስፋዬ ሻሜቦ፦** የኮሚሽነር ጽ/ቤት በዋናነት የሚያከናውናቸው ለኮሚሽነር ጽ/ቤቶች አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን ከመስጠት እና ለኮሚሽኑ ተልእኮ መሳካት አስቻይ ሁኔታዎችን በራሱ ከመፍጠር ባሻገር የተፈጠሩ አስቻይ ሁኔታዎች በተገቢ ሁኔታ ስለመከናወናቸው መከታተል፣ መገምገምና ማረጋገጥ ነው። ከዚህ አንፃር፦ በ2018 በጀት ዓመት ባለፉት ወራት ከመንግስት ለተፈቀደው በጀት የፋይናንስና የግዥ ሕጎችን እንዲሁም የንብረት አስተዳደርና ሌሎች የሚመለከቱ መመሪያዎች፣ ማኑዋሎችና ፕሮቶኮሎች መሠረት ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው በውስጥ ኦዲት ሥራ ዝርዝር ፍተሻ በማድረግ በሕጎችና መመሪያዎች መሠረት በትክክል ስለመፈጸሙ የማረጋገጥ እና በአፈፃጸም ሂደት የተስተዋሉ ሕግና መመሪያ ጥሰቶችና ሌሎች ችግሮች ካሉ በመለየት እንዲታረሙና እንዲስተካከሉ ምክረ ሃሳቦችን ማቅረብና ተግባራዊነታቸውን ከማረጋገጥ አንጻር የ2017 በጀት ዓመት የ3ኛ እና 4ኛ ሩብ ዓመት እንዲሁም የ2018 በጀት ዓመት የ1ኛ እና 2ኛ ሩብ ዓመት የፋይናንስ እንቅስቃሴ ላይ የውስጥ ኦዲት ሥራ በማከናወን ሪፖርት ለገንዘብ ሚኒስቴር ተልኳል።

የኮሚሽኑ ካፌቴሪያ አገልግሎት የፋይናንስ እንቅስቃሴ (የገቢና ወጪ ሂሳብ) እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት ድረስ ያለውን በማጣራት ሪፖርት እየተዘጋጀ ነው። ከሐምሌ 1 ቀን 2018 ዓ.ም እስከ ግንቦት 30 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ ከመንግስት የተፈቀደው በጀት ምን ያህሉ ከገንዘብ ሚኒስቴር እንደተለቀቀና ወደ ኮሚሽኑ የባንክ ሂሳብ ገቢ ስለመደረጉ እና ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ ከተደረገው በጀት ምን ያህሉ ጥቅም ላይ እንደዋለና ምን ያህሉ በጀት ከገንዘብ ሚኒስቴር እንዳልተወሰደ በኦዲት የማረጋገጥ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል።

ኮሚሽኑ በሕግ የተሰጠውን ተልእኮ በቅልጥፍናና በብቃት ለማሳካት እንዲችል እውቀትና ክህሎት ያለው የሰው ኃይል ለማሟላት 10 የሰው ኃይል በተመሳሳይ ደረጃና ደመወዝ በዝውውር ማስገባት ተችሏል። ለ40 የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ምደባ ተሰጥቷል። የሰው ኃይል መረጃዎችን ከማስተዳደር በተጨማሪ አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን በቅልጥፍና ለመስጠት በታቀደው መሠረት 26 ሰራተኞች የጡረታ መለያ ቁጥር እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን፣ ወደ ኮሚሽኑ በዝውውር ለተቀላቀሉ ባለሙያዎች፣ ለ69 ሴት ሠራተኞችና ለ29 ግቢ ውበትና ደህንነት ሠራተኞች የመፈጸም አቅም ለማሳደግ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ተሰጥቷል። 4 ባለሙያዎች የውጭ አገር የትምህርት ዕድል የተሰጣቸው ሲሆን፣ 3ቱ ውጭ አገር (ቻይና) በመማር ላይ እና አንዱ ለመሄድ በሂደት ላይ ይገኛል፡ ፡ የ164 ሠራተኞች በICSMIS ሲስተም መረጃ የማስገባት ሥራ ተከናውኗል። ያልተሟላ የትምህርት ማስረጃ ያላቸው ከተባሉት 9 ሠራተኞች እንዲያሟሉ ክትትል በማድረግ 7ቱ አሟልተዋል።

የ2017 ሁለተኛው አጋማሽና የ2018 የመጀመሪያ ስድስት ወር የዕቅድ አፈጻጸምና የሥራ ሥነምግባር ምዘና ተካሂዷል። የግራንድ አፍሪካ የተቋማትና አመራሮች ሽልማት ድርጅት ባካሄደው ምዘና ኮሚሽኑ የወርቅ ዋንጫና ዲፕሎማ ተሸላሚ የሆነ ሲሆን፣ በ2017 በጀት ዓመት የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው 15 አመራሮችና ሠራተኞች የዲፕሎማ፣ የሰርቲፊኬት እና የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ ሆነዋል።

ኮሚሽኑ በ2018 በጀት ዓመት ውስጥ ተግባራዊ የሚያደርጋቸውን ስትራቴጂዎች፣ ግቦችንና ተግባራትን መጀመሪያ ለሥራ ክፍሎች በማውረድ ቀጥሎም እስከ ሠራተኞች ድረስ እንዲወርድና ለሠራተኞች በቂ ግንዛቤ እንዲይዙ በማድረግ ወደ ተግባር እንዲገቡ ተደርጓል። የሥራ ክፍል የሥራ ኃላፊዎች በየሳምንቱና በየወሩ የባለሙያዎችን ዕቅድ አፈጻጸም በመከታተልና በመገምገም ግብረ መልስ እንዲሰጡ ክትትል እየተደረገ ነው። በእቅድ ትግበራ ሂደት ላይ የሚያጋጥሙና የታሰበው ዕቅድ በተያዘው ጊዜና መጠን እንዳይከናወን እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ 12 ቅሬታዎች እንዲሁም ቁጥራቸው 10 የሆኑ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየት በክትትል እንዲሻሻሉ ተደርጓል።

የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ከኮሚሽኑ የወሰዱትን ስትራቴጂዎች፣ ግቦችና ተግባራትን በሥራ ሥነምግባራቸው ተክነው እንዲተገብሩ እንዲሁም የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞችን የሥራ ሥነምግባር መከተል፣ የሚያጋጥሙ የሥነምግባር ጥሰቶች ላይ ወቅታዊ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ የሥነምግባር መከታተያ፣ የሕግ አገልግሎት፣ ኦዲት እና የተቋማዊ ለውጥ የሥራ ክፍሎች ተቀናጅተው በመከታተል ለሚገጥሙ ችግሮች ወቅታዊ መፍትሄ እንዲሰጥ በማድረግ 3 የቅንጅት ሥራ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡ ፡ በሥራ አፈጻጸም ሂደት ላይ ሊገጥሙ የሚችሉ ብልሹ አሠራሮችን በጥናት በመለየት በየጊዜው የማሻሻያ ምክረ ሃሳብ እየተሰጠ ይገኛል።

ኮሚሽኑ የበጀት ዓመት ዕቅዶች (የሥራና የበጀት) በቅልጥፍና እንዲከናወኑ በየጊዜው በመከታተል፣ በመገምገምና ግብረመልስ ከመስጠት ባሻገር ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደው በጀት ከሥራ ጋር በተጣጣመ መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውል ወርሃዊ በጀትን ከገንዘብ ሚኒስቴር በማስለቀቅ ወደ ኮሚሽኑ የባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲሆን ተደርጓል። የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድን ጨምሮ የሦስቱም ሩብ ዓመታት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለባለድርሻ አካላት ተልኳል። የ2016-2018 መካከለኛ ዘመን ዕቅድ አፈጻጸም በመገምገም የ 2019-2021 መካከለኛ ዘመን ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር ተልኳል።

የኮሚሽኑን የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ሥራዎችን በተመለከተ በድምሩ ከ300 በላይ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል የግንዛቤ መልዕክቶች፣ ዜናዎች እንዲሁም በየወሩ 2 ጊዜ የሚወጣ የፀረ-ሙስና ጋዜጣ በድምሩ 22 የዲጂታል ፀረ-ሙስና ጋዜጦችን ይዘት፣ አርትኦትና ዲዛይን ሥራ በመሥራት በማኅበራዊ ሚዲያ ለሕብረተሰቡ ተደራሽ የተደረገ ሲሆን፣ የኮሚሽኑን ድረገጽ (www. feac.gov.et) በአዲስ መልክ በማሻሻል ወቅታዊ

መረጃዎችን ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በርካታ የሚዲያ ሞኒተሪንግና ሁነቶች ተከናውነዋል፡፡

ኮሚሽኑ እንደ ተቋም የወንጀል ጉዳዮች ክትትል በማድረግ ከፍርድ ቤት ለሚሰጡ የተለያዩ ትእዛዞችም ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም በኮሚሽኑ የሚከናወኑ ግዥዎች ሕግን መሠረት አድርገው እንዲፈፀሙ ከ30 በላይ የሆኑ የግዥ የውል ስምምነት ሰነዶች ተዘጋጅተው ለሚመለከተው የሥራ ክፍል የቀረቡ ሲሆን፣ ከሁሉም የሥራ ክፍሎች በሚገቡ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሕግ ምክር አገልግሎት በመስጠት ሥራዎች ሕግን መሠረት በማድረግ እንዲከናወኑ ተደርጓል፡፡

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** የኮሚሽኑን ዓመታዊ ዕቅዶች ከመከታተል፣ ከማስተባበርና ከኮሚሽኑ መመሪያዎች አንጻር ጽሕፈት ቤትዎ የነበረው ሚና ምን ይመስል ነበር? የነበሩበትስ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ምንድን ናቸው?

**አቶ ተስፋዬ ሻሜቦ፦** ጽ/ቤቱ የኮሚሽኑን የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድ በማቀድ እያከናወነ ሲሆን፣ ሁሉም የሥራ ክፍሎች ያቀዱትን ተግባራት በ6 ፕሮግራም ከተፈቀደው በጀት ጋር በማጣጣም እንዲያከናወኑ እንዲሁም በየሥራ ክፍሎች የሚገኙ ባለሙያዎች የሥራ ክፍሉ ከኮሚሽኑ የወሰደውን ዕቅድ እንደ ሥራ መደባቸው በመውሰድ እንዲያቅዱ፣ ባለሙያዎች ያቀዱትን ዕቅድ ደግሞ በወርና በሳምንት ከፋፍለው አቅደው ሲተገብሩ የቅርብ ኃላፊው የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ በማካሄድ ግብረመልስ መስጠቱን በየወሩ የመከታተል፣ የመገምገምና የማረጋገጥ ሥራ በትኩረት እተከናወነ ነው፡፡ በዚህም የሥራ ክፍሎች ለ2018 በጀት ዓመት ለየሩብ ዓመቱ ያቀዱትን ተግባራት በተያዘው ጊዜና መጠን ስለማከናወናቸውና አለማከናወናቸው በማረጋገጥ ወደኋላ የቀሩትን ተግባራት በትኩረት እንዲያከናውኑ ግብረመልስ ተሰጥቷል፡፡ የሥራ ክፍሎች ያቀዱትን ተግባራት በተያዘው ጊዜና መጠን ማከናወን መቻላቸው በጠንካራ ጎን ይወሰዳል፡፡

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** የጽሕፈት ቤቱ ከውስጥ የሥራ ክፍሎች (ከዘርፎች) እና ከባለድርሻ አካላት ጋር የነበረው የሥራ ግንኙነትና የመረጃ ፍሰት ምን ያህል ውጤታማ ነበር? የተፈጠሩ መልካም ተሞክሮዎች ካሉ ቢጠቅሱልን?

**አቶ ተስፋዬ ሻሜቦ፦** ኮሚሽኑ ተልእኮው የሕብረተሰብና የመንግስት ችግር የሚሆነውን የሙስና እና ብልሹ አሠራር መከላከል እንደመሆኑ መጠን ከበርካታ ባለድርሻ አካላት ጋር በትስስርና በትብብር ትግሉን ይመራል፡፡ ከዚህ አንጻር በተለይ የጽ/ቤቱ የኮሚሽኑን የሰው ሀብት አስተዳደር መረጃዎችን ለማዘመን በያዘው ዕቅድ መሠረት ከኢፌዲሪ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በትብብር የዲጂታል የሥራ ሰዓት መቆጣጠሪያ ተግባራዊ ማድረጉ፣ ሠራተኞች የአስተዳደር አገልግሎት ጥያቄዎችን (የዓመት ፈቃድና የትብብር ደብዳቤ) በዲጂታል አሠራር እንዲጠይቁ መደረጉ፣ ከመንግስት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር የሠራተኞች ጡረታ ከፋይዳ መታወቂያ ጋር የማስተሳሰርና የጡረታ መለያ ቁጥር ለሌላቸው የመለያ ቁጥር እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

እንዲሁም በየወሩ የበጀት ጥያቄዎችን ከገንዘብ ሚኒስቴር የበጀት መምሪያ በዲጂታል አሠራር በመጠየቅ የማስለቀቅ ተግባራት እንዲሁም ሠራተኞችን የትራንስፖርት አገልግሎት አጠቃቀም ከሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አውቶቡስ መጠቀሚያ መታወቂያ እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ ተሰርቷል፡፡

በተጨማሪም ከአዳማ ዩኒቨርሲቲ ጋር የኮሚሽኑን ድረ-ገጽ የማሻሻል ሥራ እንዲሁም የተለያዩ ሚዲያዎች (ኢቢሲ፣ ኢዜአ እና ፋና ሚዲያዎች) ኮሚሽኑ በሚያዘጋጃቸው መድረኮች በመገኘት እንዲዘግቡ ጥሪ ሲደርሳቸው በመገኘት የሠሯቸው ዘገባዎች፣ ከፕላንና ልማት ሚኒስቴር የመረጃዎች ልውውጦች እና ሌሎችም የባለድርሻ አካላት ግንኙነቶች ውጤታማ ነበሩ፡፡ ከኢፌዲሪ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የትምህርት ዝግጅት መረጃቸው ያልተሟላ የተባሉ ሠራተኞች፣ የጎደለ የተባለውን የትምህርት መረጃዎችን አሟልተው ለትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን እንዲያቀርቡ በኮሚሽኑ የተደረገው ያለሰለሰ ክትትል አሟልተው ማቅረባቸው በተሞክሮ የሚወሰድ ነው፡፡

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** በዚህ ዓመት የኮሚሽኑን የውስጥ አሠራር ለማቀላጠፍ፣ አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል ወይም ዲጂታላይዝ ለማድረግ ጽሕፈት ቤቱ ያስተዋወቃቸው አዳዲስ አሠራሮች ወይም የሪፎርም ሥራዎች አሉ?

**አቶ ተስፋዬ ሻሜቦ፦** ኮሚሽኑ በበጀት ዓመቱ ለሥነምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ጥናትና ክትትል ዘርፍ ተዘጋጅተውና በሕግ አገልግሎት የሕግ ቅርጽ በማስያዝ የጸደቁና ሥራ ላይ የዋሉ ሁለት ፕሮቶኮሎች ከሪፎርም ሥራዎች የሚመደቡ ሲሆን፣ የመደበኛ ሥራ ሰዓት ቁጥጥር በዲጂታል አሠራር መሆኑ እንዲሁም የኮሚሽኑ ሠራተኞችና ሥራ ኃላፊዎች የዓመት ዕረፍት ፈቃድ እና የሚፈልጉትን የአገልግሎት ጥያቄ የማቅረብ ሥራ በዲጂታል አሠራር እንዲሆን መደረጉ ጽ/ቤቱ ያስተዋወቃቸው አዳዲስ ዲጂታል አሠራሮች ናቸው፡፡

የኮሚሽኑን ድረገጽ በአዲስ መልክ በማሻሻልና አስፈላጊ መረጃዎችን በመጫን ለሕብረተሰቡ ተደራሽ መደረጉም ከዲጂታል አሠራር ማስተዋወቅ ላይ የሚወሰድ ነው፡፡

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** ካለፈው ዓመት አፈጻጸም የተወሰዱ ዋና ዋና ትምህርቶች ምንድን ናቸው? በያዝነው አዲስ በጀት ዓመትስ ጽሕፈት ቤቱ በዋናነት ትኩረት አድርጎ የሚሠራባቸው ትልልቅ ዕቅዶችና ግቦች ምንድን ናቸው?

**አቶ ተስፋዬ ሻሜቦ፦** ጽ/ቤቱ ለበጀት ዓመቱ አቅዶ የሚሠራቸው ሥራዎች በተያዘው ጊዜ፣ ጥራትና መጠን እንዲከናወኑ በዘርፍ አመራር (በክቡር ኮሚሽነር) በየጊዜው የእያንዳንዷ ተግባር አፈጻጸም ስኬት፣ ተግዳሮትና ቀጣይ አቅጣጫ በጥብቅ ዲስፕሊን በመከታተልና በመገምገም የሚሰጡት ግብረመልስ ባለሙያውና ሥራ ኃላፊው የሚያከናውነውን ሥራ በሚገባ እንዲያውቀው፣ በባለቤትነት ስሜት እንዲያከናውንና እንዲከታተል አቅም የሚገነባ ስለሆነ በትምህርትነት የሚወሰድ ሲሆን፤ የሥራ ክፍሎች በሥራ ሥነምግባር ታንጸው ከኮሚሽኑ የወሰዱትን ዕቅድ ከተፈቀደው በጀት ጋር በማጣጣም በቅልጥፍና በማከናወን ከዕቅድ በላይ የአፈጻጸም ውጤት እንዲያስመዘግቡ በትኩረት ክትትል የሚደረግበት ይሆናል፡፡

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** በበጀት ዓመቱ ውስጥ ዕቅዶችን በአግባቡ ለመተግበር በሂደት ላይ ያጋጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ምን ነበሩ? እነዚህንስ እንዴት ተወጣችኋቸው?

**አቶ ተስፋዬ ሻሜቦ፦** ጽ/ቤቱ በበጀት ዓመቱ ያከናወናቸውን ተግባራት በጥብቅ ዲስፕሊን በሚመራ አመራር በመሆኑ የጎላ ችግር ባይኖርም፤ አንዳንድ ጊዜ የሥራ ክፍሎች ያቀዱትን ተግባር የዕለት ተዕለት ዕቅድ አድርገው ለማከናወን ከእውቀትና ከክህሎት በተጨማሪ ትኩረት አለመስጠት ክፍተቶች ስለሚታዩ ከክቡር ኮሚሽነሩ የሚደረገው ክትትልና ግምገማ እንደተጠበቀ ሆኖ በጽ/ቤቱ በኩል ተገቢ የክትትልና የግምገማ ፕሮግራም በመያዝና በማከናወን ችግሮችን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፦** የዘንድሮውን በጀት ዓመት በማጠናቀቅ ላይ ነን፤ ለሚቀጥለው በጀት ዓመት ዕቅድ ከማቀድ አንጻር ዝግጅቱ ምን ይመስላል?

**አቶ ተስፋዬ ሻሜቦ፦** ኮሚሽናችን የ2016-2018 መካከለኛ ዘመን ዕቅድን በውጤታማነት በማከናወንና በማጠናቀቅ ቀጣዩን የ 2019-2021 መካከለኛ ዘመን ዕቅድ በሚቀጥለው በጀት ዓመት ማከናወን ይጀምራል፡፡

ለ2018 በጀት ዓመት የታቀዱ ተግባራት በተያዘላቸው ጊዜ ውስጥ ከታቀደው በላይ በማከናወን እንዲጠናቀቁ በኮሚሽኑ በኩል ተገቢው ክትትል እየተደረገ ነው፡፡ ለሚቀጥለው በጀት ዓመት ደግሞ ያሉት የአምስት ዓመታት ስኬቶችን፣ ተግዳሮቶችንና አቅጣጫዎችን በጥናት በመለየት ለሕብረተሰቡና ለተቋማት ተደራሽ የሚሆኑ ተግባራትን በማቀድ ለመተግበር ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡

ስለሆነም የሕዝብ ችግር የሆኑ የሥነምግባር ጥሰትና የሙስና ችግሮችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ዕቅዶችን በማቀድ ለመተግበር የፈጻሚ ባለሙያዎችን የማስፈጸም አቅም ግንባታ ሥራዎችን የመስራት፣ በዕቅዱ ላይ በቂ ግንዛቤ መፍጠርና ለሥራው በቂ በጀት የመበጀት ሥራዎች በትኩረት የሚታቀዱ ይሆናል፡፡

እናመሰግናለን!

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀን የሚዘጋጅ ጋዜጣ

ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**EARS**

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ሞባይል 0953222255
0953222299
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስኣፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

**NCRS**

## ርዕሰ -አንቀፅ

# የተቀናጀ የሙስና መከላከል ስልቶች ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል አይነተኛ ሚና አላቸው!

ሙስናን በአንድ ተቋም ወይም በቅጣት ብቻ ከመዋጋት ይልቅ፣ ችግሩን ከመሰረቱ ለመቅረፍ የተለያዩ እርስ በእርስ የሚደጋገፉ አካሄዶችን አቀናጅቶ መተግበር ላይ ማተኮር ይገባል:: ይህ ስልት በዋናነት በሥነምግባር ግንባታ፣ በሙስና መከላከል እና በህግ ተፈጻሚነት (እርምጃ) ምሰሶዎች ላይ የሚቆም ነው:: የተቀናጀ የሙስና መከላከልን ለመተግበር የተለያዩ ስልቶች መጠቀም ይገባል:: የህዝብ ግንዛቤን ማሳደግ እና የሥነ-ምግባር ግንባታ አንዱ ነው:: ሙስናን በዘላቂነት ለመከላከል ማህበረሰቡ በሙስና አስከፊነትና በሥነ-ምግባር ላይ ያለው እውቀትና አመለካከት መቀየር አለበት:: የሥነ-ምግባር ትምህርት ከታችኛው የትምህርት እርከን ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ድረስ በስርዓተ-ትምህርት ውስጥ በማካተት ታማኝ፣ ቅን እና መልካም ሥነምግባር ያለው ትውልድ መገንባት ይገባል::

ሙስናን ለመከላከል የንቅናቄና የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን በሚዲያ፣ በማህበራዊ ሚዲያዎች እና በህዝባዊ መድረኮች አማካኝነት የሙስናን ጎጂነት እና አስከፊነት ለህዝብ ማሳወቅ ያስፈልጋል:: ሙስና የሚከሰተው አሰራሮች ግልጽ ካለመሆንና ለግል ውሳኔ ሰፊ እድል በሚሰጥበት ወቅት በመሆኑ ግልጽነትና ተጠያቂነት የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችን፣ የበጀት አጠቃቀምን እና የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥን ለህዝብ ክፍት በማድረግ ሙስናን መከላከል ያስፈልጋል::

በተለይ የአገልግሎት አሰጣጥን በዲጂታል ቴክኖሎጂ በማስደገፍ ከሰው እጅ ንክኪ በመቀነስ ጉቦ የመጠየቅና የመስጠት እድሎችን ማጥበብ ያስፈልጋል:: እንዲሁም የህግ ማዕቀፎችን በማጠናከር የአገር ውስጥ እና ዓለምአቀፍ የህግ ማዕቀፎችን በማጣጣም የሙስና መከላከያ ህጎችን ማክበር እና ማስከበር ይገባል:: የህግ ማሻሻያዎች የፀረ-ሙስና አዋጆችንና ደንቦችን ከወቅታዊ የሙስና ውስብስብ ባህሪ ጋር አብሮ እንዲሄድ ያስችላሉ::

ከዚህ በተጨማሪ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን (UNCAC) እና የአፍሪካ ህብረት የሙስና መከላከልና መዋጋት ኮንቬንሽን (AUCPCC) እና ሌሎች የስምምነት መርሆች በአገር ውስጥ ህጎችና አሰራሮች ውስጥ በማካተት ሙስናን በተቀናጀ መልኩ መከላከል ይገባል:: ሙስናን በአንድ ተቋም ብቻ መከላከል ስለማይቻል የተቀናጀ አቀራረብ የሁሉንም አካላት ተሳትፎ ይጠይቃል:: ዘርፉ በግልጽነትና በፍትሀዊ ውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን መደገፍ እና የሲቪል ማህበራት በክትትል ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ ያስፈልጋል::

በአጠቃላይ፣ የተቀናጀ የሙስና መከላከል ስልት ስኬታማ የሚሆነው ተቋማትና ባለድርሻ አካላት በተናጠል ሳይሆን በቅንጅትና ትብብር ሙስናን መታገል ሲችሉ ብቻ ነው:: ስለሆነም፣ ሙስናን በመታገል ሀገራችን በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና ማህበራዊ እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች ውጤታማ የማድረግ ኃላፊነታችን መወጣት ይጠበቅብናል::

# ሳይቃጠል በቅጠል

## የባንክ ማጭበርበር ስጋቶች እና የተቀናጁ የመከላከያ ስልቶች

የፋይናንስ ተቋማት (ባንኮች፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች እና አነስተኛ ብድር ተቋማት) ለሙስና እና ለፋይናንስ ወንጀሎች የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው:: ሙስና ከመከሰቱ በፊት ለመከላከል ተቋማቱ ጠንካራ አሰራር፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት ይኖርባቸዋል::

በአሁኑ ወቅት በፋይናንስ ዘርፉ እየታየ ያለው የዲጂታል ባንኪንግ እድገት ለደንበኞች ከፍተኛ ቅልጥፍናን ያመጣ ቢሆንም፣ ከዚሁ ጎን ለጎን የተራቀቁ የማጭበርበር ስልቶች እንዲበራከቱ በር ከፍቷል:: አጭበርባሪዎች የቴክኖሎጂ ክፍተቶችን ብቻ ሳይሆን የሰዎችን የስነ-ልቦና መታለል በመጠቀም የደንበኞችን ጥሪት እያደሙ ይገኛሉ::

በመሆኑም የባንክ አገልግሎት ደህንነትን አስተማማኝ ማድረግ የአንድ ወገን ድርሻ ሳይሆን፣ የባንኮችና የደንበኞች የጋራ ጥንቃቄና የተደራጀ መከላከያ ስልት ሲኖር ብቻ የሚሳካ ነው::

ከዚህ ጋር በተያያዘ በባንክ ደንበኞች ላይ እየተፈጸመ ያለው ማጭበርበር እጅግ አሳሳቢ እና ወቅታዊ ጉዳይ ነው:: ይህ አይነቱ ወንጀል ከተለመደው የባንክ ሙስና የሚለየው የባንክ ሰራተኞች በቀጥታ ሳይሳተፉበት (ወይም ውስጣዊ መረጃን ተጠቅመው)፣ ቴክኖሎጂንና የስነ-ልቦና ማታለያዎችን በመጠቀም ደንበኞችን በቀጥታ ሰለባ የሚያደርግ በመሆኑ ነው::

ባንኮች ይህንን ችግር ከመከሰቱ በፊት ለመከላከልና ደንበኞቻቸውን ለመጠበቅ የሚከተሉትን ወሳኝ እርምጃዎች መውሰድ ይኖርባቸዋል::

የቴክኖሎጂ ደህንነትን ማጠናከር:- ደንበኞች በሞባይል ባንኪንግ ወይም በባንክ መተግበሪያዎች ሲጠቀሙ፣ ከይለፍ ቃል በተጨማሪ ወደ ስልካቸው በሚላክ የአንድ ጊዜ ኮድ (OTP) ወይም በባዮሜትሪክስ (የአይን ወይም የጣት አሻራ) ብቻ እንዲገቡ ማድረግ ያስፈልጋል::

የግብይት ገደብ:- ደንበኞች በቀን ወይም በአንድ ጊዜ ማስተላለፍ የሚችሉትን የገንዘብ መጠን ገደብ እንዲበጁለት ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ይህ ሲሆን ማጭበርበር ቢከሰት እንኳ የሚዘረፈውን የገንዘብ መጠን ይቀንሰዋል::

የማህበራዊ ምህንድስና መከላከያና ግንዛቤ መፍጠር:- አሁን እየተከሰተ ያለው ማጭበርበር አብዛኛው የሚሰራው "ሶሻል ኢንጂነሪንግ" ወይም ሰዎችን በማታለል ነው::

አጭበርባሪዎች ራሳቸውን እንደ ባንክ ሰራተኛ፣ እንደ ሪፈራል ኮድ ሰጪ ወይም እንደ እጣ አሸናፊ አድርገው በመደወል የደንበኞችን ሚስጥራዊ ቁጥር ይቀበላሉ::

ይህንን ለመከላከል ቀጣይነት ያለው የደንበኞች ግንዛቤ ማሳደጊያ ባንኮች በየቀኑ በኤስኤምኤስ (SMS)፣ በሶሻል ሚዲያ እና በሬዲዮ/ቲቪ "ባንክ በምንም አይነት ሁኔታ የይለፍ ቃል፣ የፒን (PIN) ቁጥር ወይም የኦቲፒ (OTP) ኮድ በስልክ አይጠይቅም" የሚለውን መልዕክት ደጋግመው ማስተላለፍ አለባቸው::

ደዋዩን የማረጋገጫ ስርዓት ደንበኞች ከባንክ ተደወለላቸው ሲባል እውነተኛው የባንኩ ስልክ መሆኑን የሚያረጋግጡበት ይፋዊ የባንክ የስልክ መስመሮችን ብቻ መጠቀም ይገባል:: የውስጥ ሰራተኞች ቁጥጥር:- አንዳንድ ጊዜ ማጭበርበሮች የሚሳኩት በውስጥ ሰራተኞች መረጃ አሳልፎ ሰጪነት ሊሆን ይችላል::

የመረጃ ተደራሽነትን መገደብ ማንኛውም የባንክ ሰራተኛ ሁሉንም የደንበኛ መረጃ ማየት የለበትም:: አንድ ሰራተኛ ስራውን ለመስራት የሚያስፈልገውን ያህል መረጃ ብቻ እንዲያይ መደረግ አለበት::

የእንቅስቃሴ መዝገብ ማስታወሻ:- የትኛው ሰራተኛ በስንት ሰዓት፣ የማንን ደንበኛ አካውንት እንደተመለከተ ወይም እንደቀየረ የሚመዘግብ ሲስተም መኖር አለበት::

ይህ ሰራተኞች መረጃ አሳልፈው እንዳይሰጡ ትልቅ ማስፈራሪያ ይሆናል::

አጠራጣሪ እንቅስቃሴዎችን በቅጽበት መለየት:- የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ (AI) አጠቃቀም: የደንበኛውን የተለመደ የግብይት ባህሪ (ለምሳሌ አብዛኛውን ጊዜ በየቀኑ ከ5,000 ብር በላይ የማያንቀሳቅስ ደንበኛ) ሲስተሙ ያጠናል::

በድንገት እኩለ ሌሊት ላይ 200,000 ብር ወደ ሌላ አዲስ አካውንት ለማስተላለፍ ሲሞከር ሲስተሙ ግብይቱን በጊዜያዊነት አግዶ ለደንበኛው የማረጋገጫ ስልክ እንዲደወል ያደርጋል::

በአጠቃላይ እየታየ ያለው ማጭበርበር የባንኮችን የቴክኖሎጂ ደህንነት ብቻ ሳይሆን የደንበኞችን የስነ-ልቦና መታለል ጭምር የተጠቀመ በመሆኑ፣ መፍትሄው ባንኮች ሲስተማቸውን ከማጥበቅ ጎን ለጎን ደንበኞቻቸውን በንቃት ማስተማር ሲችሉ ብቻ ነው::

የባንክ ማጭበርበርን ለመከላከል "ደህንነት የሚጀምረው በእኔ ነው" የሚለው መርህ ለሁለቱም ወገኖች ያገለግላል:: ደንበኛው በንቃት በመጠበቅ፣ ባንኩ ደግሞ ጠንካራ የቴክኖሎጂና የአሰራር ጋሻ በመዘርጋት የተቋማቱን ተዓማኒነት እና የደንበኞችን ንብረት በጋራ ማስጠበቅ ይኖርባቸዋል::

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

በዚህ ዓምድ የተለያዩ ከሙስናና ብልሹ አሠራር አንፃር በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከናወኑና ለህብረተሰቡ ከፍተኛ እውቀትና እውነተኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመኑና በሙስና ወንጀል የተመዘበረ የሀገር፣ የህዝብና የመንግስት ሀብት በማስመለስ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችንና ግንዛቤ የሚፈጠርበት እንዲሁም ሀገራችን ያፀደቀቻቸውንና እየተገበረች ያለቻቸውን የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ፣ አህጉር ዓቀፍና ቀጠና ዓቀፍ ህጎችና አፈፃፀማቸውን አስመልክቶ የተሰሩና በመሠራት ላይ ያሉ ዋና ዋና ተግባራት አጠር ተደርገው የሚቀርቡበት ነው::በመሆኑም፣ የሙስና ወንጀል የመንግስትን ሥልጣንና ኃላፊነት መከታ በማድረግ፣ የግል ወይም የሌላ ሦስተኛ ወገንን ሕገ-ወጥ ጥቅም ለማሳደድ የሚፈጸም አደገኛ ወንጀል ነው:: በተለይም ከመሬት አስተዳደር ጋር የተያያዙ የሙስና ወንጀሎች የመንግስትንና የሕዝብን ሀብት ያለአግባብ ለግል ጥቅም የሚያውሉ በመሆናቸው በሕግ በጥብቅ ያስቀጣሉ::በሕግ አግባብ የመንግስት ባለሙያዎችና የሥራ ኃላፊዎች የተሰጣቸውን ሕዝባዊ አደራ የመጠበቅ፣ ሰነዶችንና መረጃዎችን የማጣራት እንዲሁም የመንግስትን መሬት ከሕገ-ወጥ ወረራ የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው:: ይህንን ግዴታ ወደ ጎን በመተው፣ የሰነድ አልባ መረጃዎችን ማጽናትና የመንግስትን መሬት አሳልፎ መስጠት "ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀም" እና "በሥራ ኃላፊነት ላይ እያሉ የሚፈጸም የሙስና ወንጀል" (Abuse of Office) ተብሎ በሕግ ይፈረጃል:: በጥቅም ትስስር (Network) እና በተደጋጋሚ በተፈጸሙ ወንጀሎች ላይ የፍርድ ቤት የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን መዝኖ ጥፋተኝነትን ማረጋገጡ የሕግ የበላይነትን ለማስፈን፣ በሕዝብና በመንግስት መካከል መተማመንን ለመገንባት ትልቅ ሚና አለው:: ይህንን ሕጋዊ መርህ መነሻ በማድረግ በደብረማርቆስ ከተማ የተወሰነውን የቅጣት ውሳኔ ሙሉ ይዘት እንደሚከተለው ቀርቧል:: በአማራ ክልል በደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር የአብማ ክፍለ ከተማ የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ከመሬት ጋር በተያያዘ ሙያቸውንና ስልጣናቸውን ተጠቅመው በፈጸሙት የሙስና ወንጀል 10 ተከሳሾች በእስራት ተቀጥተዋል:: ተከሳሾች፣ የሰነድ አልባ መረጃን በማጽናት እና በማጽደቅ ሂደት የመንግስትን መሬት ለሌላ ግለሰብ አሳልፈው በመስጠት በፈፀሙት የሙስና ወንጀል በቁጥጥር ስር ውለው አስፈላጊውን ምርመራ በማጣራት መዝገቡን ለምስራቅ ጎጃም ዞን አቃቢ ህግ መምሪያ



መላክ መቻሉን የከተማ አስተዳደሩ ፖሊስ መምሪያ የሙስና ወንጀሎች ምርመራ ዋና ክፍል ሃላፊ ኮማንደር ጌታነህ አሰፋ ገልጸዋል::የምስራቅ ጎጃም ዞን አቃቢ ህግ መምሪያ ከፖሊስ የደረሰውን የምርመራ መዝገብ በማደራጀትና ክስ በመመስረት በህግ አግባብ ሲታይ ከቆየ በኋላ የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀን በ19/9/2018 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተከሳሾች ጥፋተኛ መሆናቸው በሰውና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል::በዚህም 1ኛ አቶ አላምር ተስፋዬ፣ 2ኛ ወ/ሮ ሀይማኖት ታሪኩ፣ 3ኛ አቶ መኳንንት ጠለለ፣ 4ኛ አቶ እንዳልካቸው፣ 5ኛ አቶ ተሻለ መብራቴ፣ 6ኛ አቶ ዮሴፍ ጌትነት እና 7ኛ አቶ ስላንተ ጥበቡ እያንዳንዳቸው በሁለት መዝገብ በ10 አመት እስራት ተቀጥተዋል:: 8ኛ ወ/ሮ ታሪክ ሞትባይኖር በተለዬ መንገድ ከግለሰቦች ጋር በመመሳጠር የቴክኒክ ኮሚቴውንና የአብይ ኮሚቴውን በማሳመን ለግለሰቦች መብት ከመፍጠር ባሻገር በራሷ ልጆች ስም የመንግስትን መሬት በማዘወር መብት የፈጠረች መሆኑን በማስረጃ በመረጋገጡ በሁለት መዝገብ በ12 አመት እንዲሁም ወ/ሮ ሶሊያና መሀሪና ወ/ሮ አብዮት እጅጉ እያንዳንዳቸው በ3 አመት እስራት መቀጣታቸውን ገልጸዋል::የሙስና ወንጀል የመልካም አስተዳደር ችግር ከመፍጠሩም በላይ በሀገር ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮችን በማስከተል በህዝብ እና በመንግስት መካከል መተማመን እና ተቀራርበው እንዳይሰሩ የሚያደርግ መጥፎ በሽታ በመሆኑ ማንኛውም ህብረተሰብ የሙስና ወንጀል ሊፈፀም መሆኑን ሲያውቅ ወይም ሲመለከት ጥቆማ በመስጠት እና ለህግ ተባባሪ በመሆን የዜግነት ድርሻቸውን መወጣት እንደሚገባ የከተማው ፖሊስ አሳስቧል::በሌላ የሙስና ወንጀል መረጃ በወላይታ ዞን በሐሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትና መገልገል የሙስና ወንጀል ክስ ቀርቦባቸው የነበሩ ሁለት ግለሰቦች በጽኑ እስራትና በገንዘብ መቀጮ ተቀጠዋል:: ተከሳሾቹ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ 1ኛ ተከሳሽ የ2ኛ ተከሳሽ ጠበቃ ሲሆን፤ 2ኛ ተከሳሽ ከአይናቴ ሎሪሶ ከተባለች ግለሰብ ጋር በነበረው የውርስ ክርክር ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 47413 በሆነው በቀን 12/06/16 ዓ.ም ለ2ኛ ተከሳሽ ውሰኔ የተወሰነ በማስመሰል ሐሰተኛ የጠቅላይ ፍ/ቤት ማህተምና የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ምክትል ፕሬዝዳንት ፊርማ ያልሆነውን በማሳረፍ ሐሰተኛ የውሳኔ ግልባጭ ለ2ኛ ተከሳሽ የሰጠ ሲሆን፣ 2ኛ ተከሳሽም የተዘጋጀውን ሐሰተኛ ውሳኔ እያወቀ በመገልገል የግል ተበዳይ አይናቴ ሎሪሶን የውርስ ክስ በመቃወም ለዳሞት ፑላሳ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረበ በመሆኑ ተከሳሾች በፈጸሙት ሐሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀትና መገልገል ወንጀል ተከሰዋል::የወላይታ ዞን ፍትህ መምሪያ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ከፍተኛ ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን የክስ መዝገብ የመረመረው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሾቹን ጥፋተኛ በማለት 2 አመት ከ9 ወር ጽኑ እስራት እና 1,000 ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል:: ይህ የቅጣት ውሳኔ ለሌሎች መሰል ድርጊት ለሚፈጽሙ አካላት አስተማሪ እንዲሆን ታስቦ የተላለፈ ነው:: ማህበረሰቡም የሙስና ወንጀልን ለመከላከልና አጥፊዎችን ወደ ሕግ ለማቅረብ የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል:: በደብረማርቆስ ከተማ የመንግስትን መሬትና የሕዝብ አደራ በመተው ሥልጣናቸውን ያለአግባብ ለግል ጥቅም ባዋሉ 10 የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ላይ የተጣለው ከ3 እስከ 12 ዓመት እና በወላይታ ዞን በሐሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትና መገልገል የሙስና ወንጀል ክስ ቀርቦባቸው የነበሩ ሁለት ግለሰቦች በጽኑ እስራትና በገንዘብ መቀጮ የሚደርስ ፅኑ እስራት፣ ኮሚሽኑ የሚያራምደውን "የሙስና ወንጀልን የመታገልና ተጠያቂነትን የማስፈን" ቁርጠኝነት በተግባር ያሳየ ነው::ውሳኔው በጥቅም ትስስር የሚፈጸሙ የሙስና ወንጀሎችን እና ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት በማጋለጥ ረገድ የሕግ የበላይነትን ያረጋገጠ ሲሆን፤ ኮሚሽኑ ዘላቂ የሥነ-ምግባር እሴቶችን ለመገንባትና የሕዝብን ሀብት ለመጠበቅ ከሚያደርገው ጥረት አንጻር፣ ሕብረተሰቡ "ሙስናን የመጸየፍና በንቃት የመጠቆም" ባህል የዜግነት ሚናውን መወጣት አለበት::

# መልካም ዜጋ

## መልካምነት ያለበት የህክምና ሙያ!

የህክምና ሙያ ከሌሎች ሙያዎች የሚለይበት በብዙ ልዩ ባህሪያት ነው፤ በተለይም ለሰው ልጅ መልካም ከማድረግ አንጻር የሚታይ ነው:: ልዩ ከሚያደርጉት ባህሪያት መካከልም ጥቂቶቹ አንደኛ የህክምና ሙያ ሕይወት ማዳን ዋና ግቡ መሆኑ ነው:: የህክምና ሙያ በቀጥታ ከሰው ሕይወት ጋር ይያያዛል:: ሌሎች ሙያዎች ቢጠቅሙም፣ የህክምና ሙያ ዋና ግቡ ሕመም መቀነስ፣ ጤና መመለስ እና ሕይወት ማዳን ነው:: ሁለተኛ ርህራሄ እና ሰብአዊነት ሲሆን ሐኪሞች ከሕመምተኞች ጋር በርህራሄ መግባባት ይኖርባቸዋል:: ሰውን እንደ ሰው መመልከት እና መንገድ ማግኘት የሙያው መሠረት ነው::

አገልግሎቱ ከገንዘብ በላይ መሆኑ፣ ሌሎች ሙያዎች ብዙ ጊዜ በትርፍ ላይ ሊመሰረቱ ቢችሉም፣ ህክምና ግን ከሰው ጤና እና ከሕይወት ጋር ስለሚያያዝ አገልግሎቱ በገንዘብ የማይለካ ነው:: ታካሚው ለሐኪሙ የሚሰጠው እምነት ህክምና ሙያ በእምነት ላይ የተመሰረተ ነው:: ታካሚዎች ሕይወታቸውን ለሐኪሞች ያስረክባሉ:: በአጠቃላይ፣ የህክምና ሙያ ከፍተኛ ሰብአዊነት፣ ርህራሄ፣ ኃላፊነት እና ሕይወት ማዳን ላይ መመስረቱ ለሰው ልጅ መልካም ማድረግ ከሚባለው አንጻር ይህ ሙያ ከሁሉም በላይ ተፈጥሯዊ እና ከፍተኛ ዋጋ ያለው ነው:: ይህን የተቀደሰ እና ከፍተኛ ሀላፊነትን የሚጠይቅ ሙያ ለመፈጸም በከፍተኛ ሙያዊ ሥነ-ምግባር የዳበሩ እና በሰብዓዊነት መርህ የሚመሩ ምስጉን ባለሙያዎች ያስፈልጋሉ::

ሀገራችን ኢትዮጵያ በሕክምናው መስክ ታላቅ አስተዋጽኦ ያበረከቱ እና እራሳቸውን እንደ ሻማ አቅልጠው የሰዎችን ህይወት ያስቀጠሉ ምስጉን ሀኪሞችን አፍርታለች:: ከእንዚህ ምስጉን የህክምና ባለሙያዎች መካከል ዶ/ር አቢይ ታደሰ የአንገት በላይ ቀዶ ህክምና ስፔሻሊስት አንዱ ሲሆኑ፣ በዚህ የጋዜጣ አምዳችን የመልክም ዜጋ ተምሳሌት አድርገን አቅርበናቸዋል:: ዶክተር አብይ ታደሰ በኢትዮጵያ




ታዋቂና ከፍተኛ ልምድ ያላቸው የጆሮ፣ አፍንጫ እና ጉሮሮ (ከአንገት በላይ) ስፔሻሊስት ናቸው:: በተለያዩ የሀገር ውስጥ የሕክምና ተቋማት ለረጅም ዓመታት ያገለገሉ ሲሆን፣ በሙያቸው ህዝባቸውን በላቀ ሙያዊ ሥነምግባር እያገለገሉ እና ለሀገራቸው የህክምና ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ:: በተለይ በሕፃናት ሕክምና ላይ የተሰማሩ ሲሆን፣ በቀን ብዙ የሕፃናት ቀዶ ሕክምና በማድረግ የሀገሪቱን የነገ ተስፋዎች የሆኑ ህጻናትን ህይወት እየቀጠሉ፤ ተስፋቸውንም እያለመለሙ ይገኛል::

ዶ/ር አቢይ ታደሰ ሙያቸውን በታማኝነት እና በቅንነት ከመፈጸም ባሻገር የህክምና ወጭ መሸፈን ለማይችሉ ዜጎች በነፃ ህክምና በመስጠት ይታወቃሉ:: ከዚህ በተጨማሪ ታካሚዎቻቸውን ወይም ህፃናትን ቀዶ ህክምናውን ከማድረጋቸው በፊት ህፃናቱ ጭንቀት እንዳይሰማቸው በሙዚቃ እያዝናኑ የሚያክሙበት መንገድ ልዩ ደርጋቸዋል:: ለዚህ በጎ እና መልካም ተግባራቸው ደግሞ በርካታ ታካሚዎች ወይም የህጻናት ወለወጆች ምስጋና እያቀረቡላቸው ይገኛል::



# ኪነ-ጥበብ

## ሥነምግባር

### ”ንጹህ ወረቀቶች‘ እና የጃፓን ”ብዕር‘

ልጅነትን ስናስበው መጀመሪያ ወደ አዕምሯችን የሚመጣው ምስል ”ነጭ ወረቀት” ነው፡፡ ገና ምንም ያልተጻፈበት፣ ቀለም ያልነካው፣ ማንኛውንም አይነት ስዕል ወይም ፅሁፍ ለመቀበል ዝግጁ የሆነ ወጥ ገጽ፡፡ በዚህ ወረቀት ላይ መጀመሪያ የሚሰፍረው ምስል ውበት ካለው፣ ወረቀቱ ያምራል፤ መጀመሪያውኑ የተዝረከረከ መስመር ካረፈበት ግን ያንን ማስተካከል ለብዙ ዘመናት የሚፈጅ ዳገት ይሆንብናል፡፡

ታዲያ ይህንን የልጅነት ”ንጹህ ወረቀት” በአግባቡ ለመጠቀም ጃፓናውያን የተከተሉት መንገድ እጅግ ያስደንቃል፡፡ አንድ የስድት(6) ዓመት የጃፓን ህጻን ለመጀመሪያ ጊዜ የትምህርት ቤት ደጃፍ ሲረግጥ፣ የሚጠብቀው እንደ እኛ ሀገር ”ሀ፣ ሁ” ወይም ”1፣ 2” ብሎ በደረጃና በፈተና አይጨናነቁም፡፡ ይልቁንም እስከ አራተኛ ክፍል (እስከ 10 ዓመት ዕድሜው) ድረስ ምንም ዓይነት ፈተናም ሆነ ውጤት የለም፡፡

ጃፓናውያን ለምን? ለሚለው ጥያቄ የሚሰጡት መልስ አጭርና ግልጽ ነው፤ ”ልጁ ከማወቁ በፊት በሥነምግባሩ ይቀረጻል፡፡ የሥነ-ምግባር አዝመራ እነዚህ የመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት ልጆቹ እንደ ወረቀት የሚታዩበትና ታላላቆቻቸው መልካም የሚሉትን ነገር ሁሉ የሚቀዱበት(የሚጽፉበት) ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ወቅት ትምህርት ቤቶች ትኩረታቸው በሶስት ዓምዶች ላይ የጸና ነው፡፡

የባህሪ ግንባታ ልጆች እንዴት መታገስ እንዳለባቸው፣ ሌሎችን እንዴት ማክበር እንደሚገባቸውና ለደካሞች ያላቸውን ርህራሄ በተግባር ይማራሉ፡፡ በጃፓን ትምህርት ቤቶች ውስጥ የጽዳት ሠራተኛ የለም፡፡ ልጆቹ የራሳቸውን ክፍል ራሳቸው ይጠርጋሉ፡፡ ምሳቸውን ተራ በተራ ለጓደኞቻቸው ያቀርባሉ፡፡ ይህ በልጅነት ልባቸው ውስጥ ”ሥራ ክብር ነው” የሚል ትልቅ ጽሑፍ ይቀርጻል፡፡ በመካከላቸው አለመግባባት ሲፈጠር መምህር ጣልቃ ገብቶ ፈራጅ አይሆንም፡፡ ልጆቹ ራሳቸው ተነጋግረው፣ ይቅርታ ተባብለውና ተቻችለው እንዲፈቱ ይበረታታሉ፡፡

የእውነተኛው ትምህርት ፈተና የሚጀምረው ልጆቹ 10 ዓመት ሞልቷቸው አራተኛ ክፍል ሲገቡ ነው፡፡ ያን ጊዜ እነዚህ ልጆች የረጋ መንፈስ ያላቸው፣ ትኩረት ማድረግ የሚችሉና “ሥርዓት” ማለት የሕይወታቸው አካል የሆነ የተገሩ ዜጎች ሆነው ይገኛሉ፡፡ ዛሬ ጃፓን በዓለም የቴክኖሎጂና የኢኮኖሚ ማማ ላይ የቆመችው፣ በወረቀት ላይ ካለው ዕውቀት በበለጠ፣ በልጆቿ ልብ ውስጥ በቀረጸችው ጽኑ ሥነ-ምግባር ነው፡፡ እኛም ልጆቻችንን እንደ ንጹህ ወረቀት ካየናቸው፣ በላያቸው ላይ የምንጽፈው ነገር ነገ ሀገርን የሚቀይር ስዕል መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ ውጤትና በደረጃ ከመወጣጠራቸው በፊት፣ ሰው በመሆንና በሥነ-ምግባር የታነጹ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ነገ የምናጭደው ሰላማዊና የበለፀገ ማህበረሰብ መዝራት ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የጃፓንን መንገድ በመከተል ትውልድን በሥነምግባር ለማነጽ በምሳሌነት በመውሰድ ቢተገበር መልካም መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ጃፓናውያን ለዓለም ቀድመው የታዩት፣ መጀመሪያ
በልጆቻቸው ልብ ውስጥ ሥነምግባርን ስለጻፉ ነው!